www.xtrapapers.com

M12/1/A1AMH/HP2/AMH/TZ0/XX

22120014

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Tuesday 15 May 2012 (morning)
Mardi 15 mai 2012 (matin)
Martes 15 de mayo de 2012 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.
- The maximum mark for this examination paper is *[25 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est *[25 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[25 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2012

www.xtrapapers.com



*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ **አንድ** ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ **ያልተመሰረተ** መልስ ከፍተኛ ነጥብ **አያስገኝም**::*

**ድራማ**

1. በአይን የሚታዩ ለምሳሌም አልባሳት፣መድረክና መብራቶች የድራማ ዋነኛ ክፍሎች ናቸው:: ያጠናሃቸውን በተለያዩ ጻህፌ ተውኔቶች የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን አስረዳ::

2. የፀሃፌ ተውኔቱ ዋነኛ ተግባር የሰውን ልጆች እንቅስቃሴ ማሳየት ነው:: በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? ያጠናሃቸውን ከሁለት ያላነሱ የተለያዩ ፀሃፌ ተውኔቶች ስራዎች በመመርኮዝ ሀሳብህን ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

3. በልቦለድ ውስጥ የድርጊቶች ቅደም ተከተል ይቀያራል:: አንዳንዴም ድርጊቶች ይቁዋረጣሉ ወይም ይፋጠናሉ:: የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህ የጊዜ ለውጥ ለልቦለዱ የተዋጣ መሆን ያደረገውን ድጋፍ አስረዳ::

4. በልቦለድ የሚገኙት ድርጊቶች በዋናነት የሚቀርቡት የደራሲውን መልእክት ወይም ጭብጥ ለማስተላለፍ ነው:: ባጠናሀቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ በምን መልክ መልእክቶቻቸውን እንዳስተላለፉ አስረዳ::

**ስነግጥም**

5. ስነግጥም የተለያየ ትርጉም ለመስጠትና በቃላት አማካኝነት ተፈላጊውን አላማ ከግብ ለማድረስ ልዩ ልዩ ቅርጽና አቀራረብን ይጠቀማል:: ባጠናሀቸው የተለያዩ ገጣምያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ውስጥ ገጣምያኑ እንዴትና ለምን አላማ ቴክኒኮቹን እንደተጠቀሙ አብራራ::

6. ስነግጥም ከሁሉም የስነጽሁፍ ዘርፎች በበለጠ ሁኔታ ቅርጽና ይዘት በከፍተኛ ሁኔታ የተሳሰሩበት ነው:: ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ ቅርጽና ይዘት እንዴት እንደተሳሰሩ አስረዳ::

www.xtrapapers.com



**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

7. የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ፀሃፍያን ግልጽ ለመሆንና ትክክለኛ ሃሳብ ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸውን ቴክኒኮች አስረዳ:: መልስህ ባጠናህቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ላይ የተመሰረተ ይሁን::

8. ያጠናህቸውን የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች መሰረት በማድረግ ደራስያኑ የአንባቢውን ትኩረት እስከመጨረሻ ድረስ ለመያዝ የተጠቀሙባቸውን የሃሳብ አገላለጽ ቴክኒኮች አስረዳ::

**አጭር ልቦለድ**

9. አጭር ልቦለድ በአብዛኛው አንድ መዋቅር ይዞ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚቀርብ ሲሆን መቼቱም አንድ ነው:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር ሀሳብህን ግለጽ::

10. አጭር ልቦለድ የአንድን ጀግና ሁለት ገጽታ የሚያሳይ ሲሆን የጀግናው አንዱ ገጽታው ከሌላው ጋር ጦርነት ያካሂዳል:: የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት ባጠናህቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ምሳሌነት አስረዳ::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

11. ስነጽሁፍ አንባብያን የሚያውቁትንና እንግዳ የሆነውን አለም እንዲረዱ የሚያደርግ የፈጠራ ስራ ነው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ::

12. ስነጽሁፍ ስሜታችንንና ህዋሳቶቻችንን በአንድነት የሚያንቀሳቅስ ሲሆን የውጪውን አለም እንድንረዳ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በደመነፍስ የምናገኛቸውን ግንዛቤዎች እንድናጣጥም የሚያደርገን ነው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ አብራራ::

13. ስነጽሁፍ በተለያየ እድሜና ዘመን ያሉና የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች ስለተፈጥሮና ስለገጠመኞቻቸው በተመሳሳይ ሁኔታ የሚነጋገሩበት የፈጠራ ስራ ነው:: ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ::

14. ለውጥና አጋጣሚ በስነጽሁፍ ስራዎች ውስጥ ትልቅ ስፍራ አላቸው:: ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ከሁለት ያላነሱ ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ ለውጥና አጋጣሚን እንዴትና ለምን እንደተጠቀሙባቸው ግለጽ::